**አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች የቤተሰብ ህይወት ትምህርት ላይ የወላጆች በምርጫ የማስተማር ፎረም - 9ኛ ክፍል**

የተማሪው ስም : ________________________________ስልክ ቁጥር: ___________________
የአስተማሪው ስም: ________________________________ቀን : _______________________

እኔ እዚህ ያለሁት ከተዘረዘሩት አላማዎች ውስጥ ልጄ እንዳይሳተፍ የምፈልግበትን ምርጫ እንዳደርግ ነው። ልጄ እንዳይሳተፍ በማደርግባቸው አላማዎች ላይ፣ ልጄ ያለምንም ተፅእኖ አማራጭ አሳይመንቶች እንደሚሰጡት ተረድቻለሁ። ልጄ አሳይመንት በሚሰራበት እና ለአሳይመንቱ ውጤት በሚሰጥበት ወቅት፣ በትምህርት ቤቱ ህጎች እና ፖሊሲዎች መመራት እንደሚጠበቅበት ተረድቻለሁ።

**<u>አቅጣጫዎች</u>:** እባክዎ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አላማዎች ላይ ልጅዎ እንዳይሳተፍበት የሚፈልጉትን ነገር ካለ ምልክት ያድርጉበት።

___ **9.1 ተማሪው የሰው ልጅ እድገት እና የሕይወት ዑደትን ይረዳል።**
<u>መግለጫ</u>: ስለ ሕይወት ኡደት ደረጃዎች ማለትም፤ ስለ ቅድመ ወሊድ፣ ህጻንነት፣ ታዳጊነት፣ ቅድመ መዋዕለ ህጻናት፣ ትምህርት ቤት ዕድሜ፣ ጉረምስና፣ ወጣትነት፣ ጎለማሳ እና የአዛውንትነት ዕድሜ ያሉ መረጃዎች ልጅ ወልዶ ማሳደግ ስላለው ውስብስብነት እና ወላጅ ለመሆን ስለሚያፈልገው ብስለት ጋር ይያያዛል። ይህ መረጃ ተማሪዎች የራሳቸውንም ዕድገትም እነዲያደንቁ ይረዳል።

___ **9.2 ተማሪው ስለ ቤተሰብ እንደ ማሕበረሰብ አካል ስላለው ጥቅም እና እራሱም እንደ ቤተሰብ አባል ስላለው ሃላፊነት ያስረዳል።**
<u>መግለጫ</u>: ይህ ርዕስ ስለ ቤተሰብ ተግባር፤ ስለ ቤተሰብ አይነት፣ ስለ ቤተሰብ ጥንካሬ፣ ቤተሰብ ማሕበረሰቡ ላይ ስለሚኖረው ተጽዕኖ፣ እንዲሁም ስለ ቤተሰብ ግንኙነት ዋጋ የሚገልጹ መመርያዎችን ያካትታል። ጋብቻ ለ ግለሰብ እንዲሁም ለማሕበረሰቡ የሚኖረው ጥቅም፣ ፈተናዎች፣ ሀላፊነት እንዲሁም ስለዋጋው ይካተታል።

___ **9.3 ተማሪው ስነ-ወሲብ የማንነት አንድ አካል እንደሆነ ይገነዘባል።**
<u>መግለጫ</u>: ይህ መግለጫ ሥነ ወሲባዊ ማንነት እድገት ላይ ትኩረት ያረጋል። ውስጣዊ እንዲሁም ውጫዊ ግጭቶች ስነ ወሲባዊ ማንነት ጋር የተያያዙ ችግሮች ጋር ያላቸው ግንኙነት ይዳሰሳል።

___ **9.4 ተማሪው ስለ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ይመለከታል፤ እንዲሁም ይተገብራል።**
<u>መግለጫ</u>: ተማሪዎች የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችን እንዲሁም የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን በተግባር ይማራሉ። ትኩረት የሚሰጠውም ስለ ቤተሰብ ድጋፍ አስፈላጊነት፣ የቤተሰብ እና የራስ ማንነት ዋጋ፣ ዕውቀት፣ አወንታዊ የአዕምሮ ጤና ተግባራት፣ እነዲሁም ምክንያታዊ ስለሆነ ውሳኔ አሰጣጥ ነው።

___ **9.5 ተማሪው ስለ ፍቅር ግንኙነት ምንነት እና አስፈላጊነት ይመለከታል**
<u>መግለጫ</u>: የሚካተቱ ርዕሶችም የፍቅር ግንኙነትን የተመለከቱ የቤተሰብ መመርያዎች፣ የፍቅር ግንኙነት አስፈላጊነትን፣ እነዲሁም ከግንኙነቱ የሚመጡ ጫናዎችን ስለመቋቋም ናቸው። ተማሪዎች የፍቅር ግንኙነት ውስጥ ሊኖር ስለሚችል ጥቃት፣ ጾታዊ ጥቃት፣ አካላዊ እና አዕምሮዊ ጉዳት ስላላቸው ግንኙነቶች፣ እነዲሁም ከጾታዊ ግንኙነት በፊት ስልሚኖር ፍቃደኝነት ትርጉም እና ህግ ይመለከታሉ። ይህ ርዕስ ከጥንድ ብቻ ይልቅ በዛ ብሎ በቡድን ጊዜ ስለማሳለፈም ሊያካትት ይችላል።

___ **9.6 ተማሪው ስለ ጾታዊ ግንኙነት የራሱን ደረጃ ማስቀመጥ እንዲሁም ወሲብን እስከ ጋብቻ ስለማቆየት ጥቅም ይማራል።**

<u>መግለጫ</u>: ወሲባዊ ግንኙነትን ከጋብቻ በፊት መፈጸም ስለሚኖረው አካላዊ፣ ስሜታው፣ ማሕበረሰባዊ፣ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎች በማስተማር እንዲሁም ተማሪው የአቻ ግፊትን ተቋቁሞ ' አይሆነም' ማለትን እና በራሱ ምርጫ ባህሪውን እንዲከተል ይረዳዋል። መመሪያዎቹ ስለ ፍቃደኝነት ህግ እና ምንነት ይዳስሳሉ። ዋና ትኩረት የሚሰጠው ከ ጾታዊ ግንኙነት በፊት ስለሚኖር ፍቃደኝነት ነው።

___ **9.7 ተማሪው ስለ ጾታዊ ጥቃት፣ መደፈር(በፍቅር አጋርም ጨምሮ)፣ በስጋ ዘመዶች መሀል ስለሚፈጸም ወሲብ፣ወሲባዊ ማባበል፣ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ፣ ኤሊክትሮኒክ በሆነ መንገድ የሚፈጸም ጾታዊ ጥቃት ሰላለው ተጽዕኖና ስለመከላከያ መንገዶቹ ይተረጉማሉ**

<u>መግለጫ</u>: ይህ ስለ ክርክር ችሎታ፣ ግጭት አፈታት፣ አስጊ ሁኔታዎችን ስለመከላከል እና በህብረተሰቡ ውስጥ ስለሚኖር ማማከር አገልግሎቶች ይመለከታል። እነዚህን ነጥቦች ከማወቅም በተጨማሪ ተማሪው ለሌላው ያስረዳል። ተማሪው አካላዊ እና አዕምሮዊ ጎጂ የሆኑ ግንኙነቶችን በተገቢው መንገድ እነዴት እነደሚያስተናግድ ያሳያል። ተማሪው ተገቢ የሆነና ያለሆነ የኤሌክትሮኒክ ዕቃ አጠቃቀምን ይለያል። መመርያው አንድን ሰው ለ ወሲብ ንግድ ማግባባት ስለሚኖረው ህጋዊ አንደምታ ያካትታል። በተጨማሪም ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ተጠቂዎችን ስለመለየት፣ የዝውውሩን አይነት ስለመረዳት እነዲሁም እንዴት በማይጎዳና ሀላፊነት በተሞላበት መልኩ ጥቆማ ማቅረብ እነደሚቻል ያካትታል።

___ **9.8 ተማሪው ስለ ንጥረ ነገር አጠቃቀም እና ተገቢ ስላልሆን አጠቃቀም የተለዩ መረጃዎችን ከእያንዳነዱ የሕይወት ደረጃ ጋር አያይዞ ይረዳል።**

<u>መግለጫ</u>: የዚህ ርዕስ ትኩረት የሚሆነው በ እርግዝና ወቅት እና በጉረምስና ወቅት ስለሚኖር ንጥረ ነገር አጠቃቀም እና ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም በዕለት ተእለት ተግባር የሚኖረው ተጽዕኖ ላይ ነው።

___ **9.9 ተማሪው ስለ ስነ-ተዋልዶ ሒደት ለማስረዳት ይችላል።**

<u>መግለጫ</u>: የአካል ክፍሎች ጥናት፣ ፊዚዮሎጂ፣ ጽንስ፣ የጽንስ እድገት፣ ወሊድ፣ ቅድመ ወሊድ እንክብካቤ በዚህ ስር የተካተቱ ናቸው።

___ **9.10 ተማሪው ራስን መመርመርን ጨምሮ የተለዩ የጤና ሁኔታዎችን መረዳቱን ያሳያል።**

<u>መግለጫ</u>: ትኩረቱ የሚሆነው የወር አበባን የተመለከተ ትክክለኛ የሆነ መረጃ፣ ንጹህ ስለሆነ የንጽህና መጠበቂያ ውጤቶች አጠቃቀም፣ ቅድመ ወር አበባ ምልክቶች፣ ማረጥ፣ ጾታን መሰረት ያረጉ ጭንቀቶች ላይ ነው። ራስን በመፈተሽ ራስን ከበሽታ መጠበቅ በተለይም ጡት እና የዘር ከረጢትን በመፈተሽ ራስን መመርመርን ይጨምራል።

___ **9.11 ተማሪው እርግዝናን ስለመከላከል እና በሽታን ስለመቆጣጠር ያለውን እውቀት ያሳያል።**

<u>መግለጫ</u>: ርዕሱ የሚያካትተው ስለ አዋቂነት ግንኙነት አመሰራረት፣ የቤተሰብ ዕቅድ ወቅት ግምት ውስጥ ስለሚገቡ ነጥቦች፣ የእርግዝና መከላከያዎችን የተመለከቱ ትክክለኛ ያልሆኑ አመለካከቶች፣ ከእርግዝና መከላከልና በሽታ መቆጣጠር አንጻር የ እርግዝና መከላከያዎች ውጤታማነት፣ እና ከ እርግዝና መከላከያ መንገዶች ጋር የተያያዙ ውሳኔዎችን ነው። ውርጃ እነደ ወሊድ መቆጣጠርያ አይቀርብም፤ ነገር ግን ድንገተኛ የሆነ ውርጃ ወይም የጽንስ መጨናገፍ ይብራራል እንዲሁም በፍላጎት የሚደረግ ጽንስ ማቋረጥ ጉዳዮቹ ይተነተናሉ።

___ **9.12 ተማሪው ስለ ኤች. አይ.ቪ. ቫይረስ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶች ያብራራል።**
<u>መግለጫ</u>: ይህ የ ኤች. አይ.ቪ. ቫይረስ መተላለፊያ እና መከላከያ መንገዶች ምልከታ ነው።

___ **9.13 ተማሪው የመድሎ ውጤቶችን ይለያል።**
<u>መግለጫ</u>: መምህሩ ተማሪዎች ስለ መድሎ አይነቶች እና በገለሰብም ሆነ በ ቤተሰብ ሕይወት ላይ ያለውን ተጽዕኖ ለይተው እንዲያውቁ ይረዳቸዋል። ውይይቱ ትኩረቱን የሚያደርገው በግለሰቦች እንዲሁም በ ቤተሰቦች መካከል ስለሚኖር ልዩነት ጥቅም እና ዋጋ ነው። መድሎ በግለሰብ አዕምሮዊ ጤና ላይ ስለሚኖረው ተጽዕኖም ይዳሰሳል።

___ **9.14 ተማሪው የትምሕርትና የስራ ግቦችን መለየት ይጀምራል።**
<u>መግለጫ</u>: ተማሪዎች የትምሕርትና የስራ አላማዎችን (ግቦችን) ያዘጋጃሉ። 'የሕይወት ግብ' የተሰኘው ፕሮጀክት ተማሪዎች ያዘጋጁትን ግብ ከውጤት የሚያደርሱበትን መዋቅር የያዘ ሲሆን ተማሪዎችም የተለያዩ የማንነትና የስራ አማራጮችን የሚመለከቱበት ተገባራትን ያከናውናሉ። ተማሪዎች የማህበራዊ ግንኙነት ድሕረ-ገጾችን መጠቀም የስራ ግባቸው ላይ ያለውን ተጽዕኖም ይወያያሉ።

___ **9.15 ተማሪው ስለ እርግዝና መከላከልና በሽታ መቆጣጠር ያሉ እውነታዎችን በድጋሚ ይመለከታል።**
<u>መግለጫ</u>: የእርግዝና መከላከያዎች ውጤታማነታቸው ከእርግዝና መከላከልና በሽታ መቆጣጠር አንጻር ይተነተናሉ። በዚህም እርግዛናን እና በግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከል ሙሉ ለሙሉ ውጤታማ የሆነው መንገድ መታቀብ መሆኑ በሰፊው ይገለጻል።

**ትምህርት ቤታችሁ በወሰነው ቀን መሰረት ይህንን ቅፅ በመሙላት ለርእሰ-መምህሩ እባክዎን ያስረክቡ**

የወላጅ/የአሳዳጊ ፊርማ: ________________________________________ ቀን: __________